QAFILA

ቃፊላ የጉዞ ወኪል

# የዑምራ
# አፈፃፀም መመሪያ



ከዝግጅት እስከ ዑምራ ማጠናቀቅ

ኢሕራም | ጠዋፍ | ሰዕይ | ፀጉር

Qafila Tour & Travel

0938383802 | 0970707011

# ማውጫ

የዑምራ መመሪያ

| | | |
|---|---|---|
| 01 | መግቢያ | 5 |
| 02 | የጉዟችን መሪ የነብዩ ፈለግ | 6 |
| 03 | ከኢሕራም በፊት ዝግጅት | 7 |
| 04 | ኢዛር እና ሪዳእ | 9 |
| 05 | ኒያ እና ኢሕራም መጀመር | 12 |
| 06 | አምስቱ የሚቃት ስፍራዎች | 14 |
| 07 | ሚቃትን በተመለከተ ማስታወሻ | 16 |
| 08 | ተልቢያ | 19 |
| 09 | የተልቢያ ትሩፋት | 20 |
| 10 | የኢሕራም ክልከላዎች | 22 |
| 11 | በኢሕራም የሚፈቀዱ | 24 |
| 12 | የመካ እና የሐረም ክብር | 26 |
| 13 | ወደ መስጂደል ሐረም መግባት | 28 |
| 14 | ጠዋፍን መጀመር | 30 |

# ማውጫ

የዑምራ መመሪያ

| | | |
|---|---|---|
| 15 | የጠዋፍ ሱናዎች | 32 |
| 16 | በጠዋፍ ጊዜ የሚባል ዱዓ | 34 |
| 17 | በጠዋፍ ጊዜ ማስተንተን | 35 |
| 18 | የሐጀረል አሰወድ ትሩፋት | 36 |
| 19 | መቃመ ኢብራሂም እና ሶላት | 38 |
| 20 | ዘምዘም መጠጣት | 40 |
| 21 | በሶፋ እና በመርዋ መካከል ሰዕይ | 42 |
| 22 | የሶፋ እና የመርዋ ዚክር | 44 |
| 23 | የሰዕይ ዚክር የንባብ አገዛ | 46 |
| 24 | ሰዕይ እና የተሰፋ ትምህርት | 47 |
| 25 | ፀጉር መቁረጥ እና መፈታት | 49 |
| 26 | ለሴቶች እና ለቡድን ተጓዦች | 51 |
| 27 | የዑምራ አጭር ማጠቃለያ | 53 |
| 28 | የጉዞ ማረጋገጫ እና ማስታወሻ | 55 |

# ማውጫ

## የተመረጡ ዱዓዎች

| | | |
|---|---|---|
| 29 | 1. የደከመ ልብ ጥሪ | 56 |
| 30 | 2. በቃላት ያልተገለጡ ሐጃዎች | 57 |
| 31 | 3. ለአዲስ ጅማሮ | 58 |
| 32 | 4. የሕይወት ጥረት ፍሬ እንዲያፈራ | 59 |
| 33 | 5. የወላጆችን ውለታ በዱዓ ማስታወስ | 60 |
| 34 | 6. ለቤተሰብ ሰላምና ለልጆች መልካምነት | 61 |
| 35 | 7. ለዕዳ፣ ለኑሮ ጭንቀትና ለሐላል ሲሳይ | 62 |
| 36 | 8. ለታመሙ ሰዎችና ለአስታማሚዎቻቸው | 63 |
| 37 | 9. ዱዓ እንድናደርግላቸው ለጠየቁን | 64 |
| 38 | 10. ለተበደሉ፣ ለተፈናቀሉና ለተራቡ | 65 |
| 39 | 11. ለማይታወቀው ነገ አላህን መታመን | 66 |
| 40 | 12. ከዑምራ በኋላ የሚቀጥል ለውጥ | 67 |
| 41 | ማጣቀሻዎች | 68 |

01 / ዝግጅት

# መግቢያ



ምስጋና ለዓለማት ጌታ ለአላህ ይሁን። በካዕባ ዙሪያ ከዞሩት፣ በሶፋና በመርዋ መካከል ሰዕይ ካደረጉት፣ አላህንም ካወሱት ሁሉ በላጭ በሆኑት በነብዩ ሙሐመድ ﷺ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ሰላምና በረከት ይስፈን።

የተከበራችሁ የዑምራ ተጓዦች፤ አላህ ይህን ታላቅ ዒባዳ እንድትፈጽሙ ስላስቻላችሁ ተደሰቱ፣ አመስግኑትም። ዑምራችሁን በቀላሉና እሱ በሚወደው መልኩ እንድትፈጽሙ እንለምነዋለን። ለእሱ ብቻ የተደረገ፣ የነብዩንም ፈለግ የተከተለ፣ በመልካም ሥራችሁ ሚዛን የሚቀመጥ ዒባዳ ያድርግላችሁ። አሚን።

ይህ መመሪያ ለቃፊላ ዑምራ ፈጻሚ ተጓዦች ተዘጋጅቷል። ቅደም ተከተሉን ለመማር፣ ዱዓዎችን ለማንበብና በጉዞ ጊዜ ለማጣቀስ ይጠቀሙበት።

ወደ ተከበረው ቤት

02 / ዝግጅት

# የጉዟችን መሪ የነብዩ ፈለግ



ለሁሉም ጉዞ መሪ፣ ለመንገድም አመላካች እንዳለ ሁሉ፣ የዑምራ ዒባዳችን መሪ ነብዩ ሙሐመድ ﷺ ናቸው። እሳቸውም፦

“لِتَأْخُذُوا مَنَاسِكَكُمْ”

“የሐጅ ሥርዓቶቻችሁን ከእኔ ተማሩ።”

ሰሒሕ ሙስሊም 1297፤ ብለዋል።

ስለዚህ አፈጻጸሙን ከታማኝ ምንጭ መማርና በማወቅ መፈጸም ያስፈልጋል። ይህ አጭር ቡክሌት የዑምራን ሥራዎች በቀላል አገላለጽ ያቀርባል። የአላህን ውዴታ እንድትፈልጉና እሱን ከሚያስቆጣ ተግባር እንድትርቁ ያስታውሳል።

ዋና ቅደም ተከተል፦ ኢሕራም፣ ጠዋፍ፣ ሰዕይ፣ ፀጉር መላጨት ወይም ማሳጠር። በእያንዳንዱ ተግባር ዚክርና ዱዓ ያብዙ።

ዒባዳ በእውቀት

# ከኢሕራም በፊት ዝግጅት



ንጽሕና • ዝግጅት

## ንሰሐ እና የሰዎች መብት

- የበደላችሁት ካለ መብቱን መልሱ፣ ይቅርታም ጠይቁ።
- ዒባዳችሁን በሐላል ገንዘብና በቅን ኒያ ለመፈጸም ተዘጋጁ።

## የአካል ንጽሕና

- ካስፈለገ ጥፍር ቁረጡ፣ የላይኛውን ከንፈር ጢም (ቀድሞ ቀመስ) አሳጥሩ፣ የብብትና የብልት አካባቢ ፀጉርን አስወግዱ።
- ይህ ሁሉ ኢሕራም ከመጀመራችሁ በፊት ይሁን።

“الْفِطْرَةُ خَمْسٌ ـ أَوْ خَمْسٌ مِنَ الْفِطْرَةِ ـ الْخِتَانُ، وَالِاسْتِحْدَادُ، وَنَتْفُ الْإِبْطِ، وَتَقْلِيمُ الْأَظْفَارِ، وَقَصُّ الشَّارِبِ”

“የፊጥራ ተግባራት አምስት ናቸው፤ ወይም ከፊጥራ ተግባራት መካከል አምስቱ፦ መገረዝ፣ በብልት አካባቢ ያለውን ፀጉር መላጨት፣ የብብትን ፀጉር መንቀል፣ ጥፍርን መቁረጥ እና ከላይኛው ከንፈር በላይ ያለውን ፀጉር ማሳጠር ናቸው።”

አልቡኻሪ 5889

- ለወንድም ለሴትም ከኢሕራም በፊት መታጠብ ይወደዳል።
- የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ያለባትንም ያካትታል።

“اغْتَسِلِي وَاسْتَثْفِرِي بِثَوْبٍ وَأَحْرِمِي”

ነብዩ ﷺ አስማእ ቢንት ዑመይስን፦ “ታጠቢ፣ በጨርቅ ደሙን ጠብቂ፣ ኢሕራምም አድርጊ” አሏት።

ሰሒሕ ሙስሊም 1218።

- መታጠብ አለመቻል ግን ሚቃትን ለማለፍ ምክንያት አይሆንም።

# ኢዛር እና ሪዳእ



ኢዛር • ሪዳእ

## የወንዶች አለባበስ

- ወንዶች እንደ ሸሚዝና ሱሪ ያሉ ልብሶችን አውልቀው ኢዛርና ሪዳእ ይለብሳሉ።
- ኢዛር ከወገብ በታች፣ ሪዳእ ከላይ የሚደረብ ጨርቅ ነው።
- በመደበኛው ሁኔታ ሁለቱም ትከሻዎች ይሸፈናሉ።

“لَا تَلْبَسُوا الْقَمِيصَ وَلَا السَّرَاوِيلَاتِ وَلَا الْعَمَائِمَ، وَلَا الْبَرَانِسَ”

“ሸሚዝ፣ ሱሪ፣ ጥምጣም ወይም ራስን የሚሸፍን ኮፍያ አትልበሱ።”

አልቡኻሪ 1838

- ወንድ ሰው ከኢሕራም ኒያ በፊት በሰውነቱ ላይ ሽቶ መቀባት ይችላል፤ በኢሕራም ልብሱ ላይ ግን አይቀባ።
- ዓኢሻ እንዲህ ብለዋል፦

“كُنْتُ أُطَيِّبُ رَسُولَ اللَّهِ ﷺ لِإِحْرَامِهِ حِينَ يُحْرِمُ”

“የአላህ መልእክተኛ ﷺ ወደ ኢሕራም ሊገቡ ሲዘጋጁ፣ ሽቶ እቀባቸው ነበር።”

አልቡኻሪ 1539

# የሴቶች አለባበስ



- ሴቶች ሰውነታቸውን የሚሸፍን ሰፊ፣ የማያሳይ ልብስ ይለብሳሉ።
- የተለየ ቀለም አያስፈልግም።
- ኒቃብና ጓንት አይለብሱም።
- ሽቶ አይጠቀሙም።

“وَلَا تَنْتَقِبِ الْمَرْأَةُ الْمُحْرِمَةُ وَلَا تَلْبَسِ الْقُفَّازَيْنِ”

“በኢሕራም ላይ ያለች ሴት ኒቃብ አታድርግ፤ የእጅ ጓንትም አትልበስ።”

አልቡኻሪ 1838

“إِذَا شَهِدَتْ إِحْدَاكُنَّ الْعِشَاءَ فَلَا تَطَيَّبْ تِلْكَ اللَّيْلَةَ”

“ከእናንተ አንዷ ለዒሻእ ሶላት ስትወጣ በዚያች ሌሊት ሽቶ አትጠቀም።”

ሙስሊም 443

05 / ኢሕራም

# ኒያ እና ኢሕራም መጀመር



- የዑምራን ዒባዳ ለመጀመር በልባችሁ አስቡ።
- ከዚያ ተልቢያን ጀምሩ፦

"لَبَّيْكَ اللَّهُمَّ عُمْرَةً"

ለበይከ አላሁመ ዑምረተን። "ጌታዬ ሆይ፤ ዑምራ ለመፈጸም ጥሪህን ተቀብያለሁ።"

- ልብሱን መልበስ ብቻ ኢሕራም አይደለም፤ ኢሕራም ወደ ዒባዳው ለመግባት በሚደረግ ኒያ ይጀምራል።

## ለሌላ ሰው ዑምራ ሲደረግ

”لَبَّيْكَ اللَّهُمَّ عُمْرَةً عَنْ فُلَانٍ“

“ጌታዬ ሆይ፤ ለእገሌ ዑምራ ለማድረግ ጥሪህን ተቀብያለሁ።” በ“ፉላን” ፋንታ የሰውየውን ስም ይጥቀሱ። ኒያው በልብ ነው፤ ይህ የተልቢያ አገላለጽ ነው። በሌላ ሰው ምትክ ዑምራ የማድረግ ሁኔታዎችን ከመሪው ጋር ያረጋግጡ።

## ከሶላት በኋላ ኢሕራም

- የግብፅ ዳር አልኢፍታእ አጭር ፈትዋ፦ ከኢሕራም በፊት ሁለት ረከዓ መስገድ ይወደዳል።
- ከግዴታ ወይም ከነፍል ሶላት በኋላ ማሕረምም ይበቃል።
- ሳይሰግዱ ማሕረምም ይፈቀዳል፤ ሶላት መስፈርት አይደለም።
- ለሶላት ብላችሁ ሚቃትን አትለፉ።

ዳር አልኢፍታእ አልሚስሪያ፣ ፈትዋ 7516

ኒያ • ተልቢያ

# አምስቱ የሚቃት ስፍራዎች




- ሚቃት ዑምራ ወይም ሐጅ ለማድረግ የሚመጣ ሰው ኢሕራም ሳያደርግ ማለፍ የሌለበት ወሰን ነው።
- ሰውየው የሚቃቱ አካባቢ ነዋሪ ባይሆንም፣ በዚያ አቅጣጫ ከመጣ ያ ሚቃት ይመለከተዋል።
- ዙልሑለይፋ፡- ለመዲናና በዚያ አቅጣጫ ለሚመጡ። አብያሩ ዓሊይ ተብሎም ይታወቃል።
- አልጁሕፋ፡- ለሻም፣ ለግብፅ፣ ለመግሪብና በዚያ አቅጣጫ ለሚመጡ። ራቢግም በዚህ መስመር የኢሕራም መነሻ ሆኖ ይጠቀማል።
- ቀርኑል መናዚል፡- ለነጅድና በዚያ አቅጣጫ ለሚመጡ። አስሰይሉል ከቢር ተብሎ ይታወቃል።
- የለምለም፡- ለየመንና በዚያ አቅጣጫ ለሚመጡ። አስሰዕዲያ ከሚለው ስም ጋር ይታወቃል።
- ዛቱ ዒርቅ፡- ለዒራቅና በዚያ አቅጣጫ ለሚመጡ።

“وَقَّتَ لأَهْلِ الْمَدِينَةِ ذَا الْحُلَيْفَةِ، وَلأَهْلِ الشَّأْمِ الْجُحْفَةَ، وَلأَهْلِ نَجْدٍ قَرْنَ الْمَنَازِلِ، وَلأَهْلِ الْيَمَنِ يَلَمْلَمَ”

“ለመዲና ሰዎች ዙል ሑለይፋን፣ ለሻም ሰዎች አልጁሕፋን፣ ለነጅድ ሰዎች ቀርን አልመናዚልን፣ ለየመን ሰዎች ደግሞ የለምለምን ወደ ኢሕራም የሚገቡባቸው ሚቃቶች አድርገው ወሰኑ።”

አልቡኻሪ 1524

“فَانْظُرُوا حَذْوَهَا مِنْ طَرِيقِكُمْ. فَحَدَّ لَهُمْ ذَاتَ عِرْقٍ”

“በመንገዳችሁ ላይ ከእርሷ ጋር (ቀርን አልመናዚል) ትይዩ የሆነውን ቦታ ተመልከቱ። ከዚያም ዛተ ዒርቅን ሚቃት አድርገው ወሰኑላቸው።”

አልቡኻሪ 1531፣ የሰይዱና ዑመር ንግግርና ውሳኔ

07 / ኢሕራም

# ሚቃትን በተመለከተ ማስታወሻ



የአየር ጉዞ ማስታወሻ

## ከኢትዮጵያ የሚጓዙ ሙዕተሚሮች

- አዲስ አበባ → ጂዳ → መካ፦ ከጂዳ ቀጥታ ወደ መካ ለዑምራ የምትሄዱ፣ አውሮፕላኑ የለምለምን ሲተያይ በአየር ላይ ኢሕራም አድርጉ።
- የሚቃቱን መድረሻ ከበረራ ሠራተኞች ጋር አረጋግጡ፤ ወደ ጂዳ እስክትደርሱ አትጠብቁ።

- ይህን ከፈራችሁ ደግሞ ማለትም አብራሪው ላያስታውስን ይችላል ብላችሁ ከፈራችሁ እዚያው ከቤታችሁ ወይም ከኤርፖርት ነይቱ።
- መዲናን በመጀመሪያ ለመጎብኘት፦ ቀጥታ ወደ መዲና ብትበሩ፣ ወይም ጂዳ ደርሳችሁ መካ ከመሄዳችሁ በፊት ወደ መዲና ለዚያራ ብትሄዱ፣ ዚያራችሁን ጨርሳችሁ ከመዲና ወደ መካ ስትጓዙ ከዙል ሑለይፋ (አብያሩ ዓሊ,ይ) ታሕርማላችሁ።
- ልብ ይበሉ፦ ሚቃት በዜግነት ሳይሆን በጉዞው መስመር ይወሰናል።
- በረራው ሌላ ሚቃት የሚተያይ ከሆነ ያንን ይከተሉ።
- ልብሳችሁን አስቀድማችሁ አዘጋጁ፤ ሚቃትን ከማለፍ በፊት ኒያ አድርጉ።

“هُنَّ لَهُنَّ وَلِمَنْ أَتَى عَلَيْهِنَّ مِنْ غَيْرِهِنَّ، مِمَّنْ أَرَادَ الْحَجَّ وَالْعُمْرَةَ”

“እነዚህ ሚቃቶች ለእነዚያ አካባቢዎች ነዋሪዎች፣ እንዲሁም ከሌሎች አካባቢዎች መጥተው በእነዚህ ሚቃቶች በኩል ለሚያልፉ፣ ሐጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ ላሰቡ ሁሉ ናቸው።”

አልቡኻሪ 1524



- በመካ ሐረም ውስጥ ያለ ሰው ለዑምራ ወደ ሒል፣ ለምሳሌ ተንዒም፣ ይወጣል።

“فَأَمَرَ عَبْدَ الرَّحْمَنِ بْنِ أَبِي بَكْرٍ أَنْ يَخْرُجَ مَعَهَا إِلَى التَّنْعِيمِ، فَاعْتَمَرَتْ بَعْدَ الْحَجِّ فِي ذِي الْحَجَّةِ”

“ከዚያም ዐብዱረሕማን ኢብን አቢ በክርን ከእርሷ ጋር ወደ ተንዒም እንዲወጣ አዘዙት። እርሷም ከሐጅ በኋላ፣ በዙልሒጃ ወር ዑምራ አደረገች።”

አልቡኻሪ 1785

### በሐረም ውስጥ ላለ ሰው፦ ወደ ዑምራ

ሐረም → ተንዒም (ከሐረም ውጭ) → ኢሕራም → መካ (ለዑምራ)

አልቡኻሪ 1785 ↗

08 / ኢሕራም

# ተልቢያ



- ከኢሕራም መጀመሪያ አንሥቶ የዑምራን ጠዋፍ እስክትጀምሩ ድረስ ተልቢያ ደጋግማችሁ በሉ።
- ነብዩ ﷺ የሚሉት፦

“لَبَّيْكَ اللَّهُمَّ لَبَّيْكَ لَبَّيْكَ لَا شَرِيكَ لَكَ لَبَّيْكَ إِنَّ الْحَمْدَ وَالنِّعْمَةَ لَكَ وَالْمُلْكَ لَا شَرِيكَ لَكَ”

“ለበይከ አላሁመ ለበይክ። ለበይከ ላ ሸሪከ ለከ ለበይክ። ኢነል ሐምደ ወኒዕመተ ለከ ወልሙልክ። ላ ሸሪከ ለክ።”

የትርጉሙ ሐሳብ፦ “ጌታዬ ሆይ፤ በፍቅርና በታዛዥነት ጥሪህን ተቀብያለሁ፤ ደጋግሜም እቀበላለሁ። አጋር የለህም። ምስጋና፣ ጸጋና ንግሥና ያንተ ናቸው፤ አጋር የለህም።”

ሰሒሕ አልቡኻሪ 1549።

# የተልቢያ ትሩፋት



ዚክር • ተልቢያ

“مَا مِنْ مُسْلِمٍ يُلَبِّي إِلَّا لَبَّى مَنْ عَنْ يَمِينِهِ أَوْ عَنْ شِمَالِهِ مِنْ حَجَرٍ أَوْ شَجَرٍ أَوْ مَدَرٍ حَتَّى تَنْقَطِعَ الْأَرْضُ مِنْ هَاهُنَا وَهَاهُنَا”

“ማንኛውም ሙስሊም ተልቢያ ሲል፣ በቀኙና በግራው ያሉ ድንጋዮች፣ ዛፎችና የአፈር ክምሮች እስከ ምድር ጫፍ ድረስ አብረውት ተልቢያ ይላሉ።”

ጃሚዕ አትቲርሚዚ 828።



“مَا أَهَلَّ مُهِلٌّ قَطُّ إِلَّا بُشِّرَ، وَلَا كَبَّرَ مُكَبِّرٌ قَطُّ إِلَّا بُشِّرَ. قِيلَ: بِالْجَنَّةِ؟ قَالَ: نَعَمْ”

“ተልቢያ ያለም ሆነ ተክቢር ያለ ሰው የምሥራች ይነገረዋል። “በጀነት ነው?” ተብለው ሲጠየቁ “አዎን” አሉ።”

አጥጠበራኒ፣ አልሙዕጀም አልአውሰጥ 7779፤ አልአልባኒ፣ አሰሲልሲላ አሰሰሒሐ 1621።

- ተልቢያ የተውሒድና የታዛዥነት አዋጅ ነው።
- እንደበታችሁ የሚለውን ልባችሁም እንዲያስተውል አድርጉ።

# የኢሕራም ክልከላዎች



## በኢሕራም ጊዜ ክልከላዎችን ይጠብቁ

- ኢሕራም ከጀመረ በኋላ የሚከተሉትን ጠብቁ፦ ፀጉርና ጥፍር፦ ሆን ብሎ ፀጉር ማሰወገድና ጥፍር መቁረጥ ይከለከላል።
- ሽቶ፦ በልብሰም ሆነ በሰውነት ላይ ሽቶ መጠቀም ይከለከላል።
- ለወንዶች፦ ራሰን በቀጥታ በሚነካ መሸፈኛ መሸፈንና እንደ ሸሚዝ፣ ሱሪ ያለ ልብሰ መልበሰ ይከለከላል።
- ነገር ግን ሰፌት ያለው ነገር ሁሉ እንደተከለከለ አትረዱ።
- ለሴቶች፦ ኒቃብና ጓንት መልበሰ ይከለከላል።

- ፊትን በሌላ መሸፈኛ ስለመሸፈን የፊቅህ ዝርዝር አለ፤ መሪውን ጠይቁ።
- ጋብቻና ግንኙነት፦ የጋብቻ ውል ማድረግና ለሌላ ማስደረግ ይከለከላል።
- ከማጨት፣ ከሰሜት ንክኪና ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ራቁ።

አልቡኻሪ 1838፤ ሙስሊም 1409

- ክልከላ ከተፈጸመ እንደ ተግባሩ፣ እንደ ዕውቀትና እንደ ሁኔታው ፍርዱ ይለያያል።
- የቡድኑን የሃይማኖት መሪ አማክሩ።

“وَلَا تَلْبَسُوا شَيْئًا مَسَّهُ زَعْفَرَانٌ، وَلَا الْوَرْسُ”

“ዘዕፈራን ወይም ወርስ የተቀባ ልብስ አትልበሱ”

አልቡኻሪ 1838

“لَا يَنْكِحُ الْمُحْرِمُ وَلَا يُنْكَحُ وَلَا يَخْطُبُ”

“ሙሕሪም አያገባም፣ አያጋባም፣ አያጭም”

ሙስሊም 1409

# በኢሕራም የሚፈቀዱ



መነጽር የገንዘብ ቦርሳ ጃንጥላ

- ኢሕራም ውስጥ ሆናችሁ ሰዓት፣ የጆሮ መስሚያ መሣሪያ፣ ቀለበት፣ መነጽር፣ የገንዘብ መታጠቂያና ቦርሳ መጠቀም ትችላላችሁ።
- ለወንዶች ተገቢ የሆነ ክፍት ጫማ መጫማትም ይፈቀዳል።
- በጃንጥላ፣ በመኪና ጣራና በሕንፃ ጥላ መጠለል፣ ዕቃ መሸከምና ቁስል ማሰር ይቻላል።
- ሕክምና ወይም የተለየ መሸፈኛ ካስፈለገ ሁኔታውን አስታውቁ።
- ልብስን መለወጥና ማጠብ፣ ሰውነትንና ራስን መታጠብ ይፈቀዳል።

- ሽቶ ያልተጨመረበትን የንጽሕና ዕቃ መምረጥ ይመከራል።
- በመታጠብ ጊዜ ያለ ፍላጎት የሞተ ፀጉር ቢወድቅ ሆን ብሎ መቁረጥ ጋር አንድ አይደለም።
- ወንድ ሰው ረስቶ ራሱን ከሸፈነ ሲያስታውስ ወዲያው ይግለጥ።
- ስለ ካሳ ዝርዝር ዐሊምን ይጠይቅ።
- ኢሕራም ሶላትን አያስቀርም።
- የኢሕራም ሁለት ረከዓ የሱና ጉዳይ እንጂ የኢሕራም ግዴታ አይደለም።

# የመካ እና የሐረም ክብር



- መካ ወሕይ የወረደባት፣ የነብዩ ﷺ የትውልድ ከተማ፣ ዘምዘም የፈለቀባትና ሙስሊሞች በሶላት የሚቅጣጩት ካዕባ ያለባት ቅዱስ ከተማ ናት።
- የመካ ሐረም ለሙስሊሞች የተለየ ሰፍራ ነው፤ ሙስሊም ያልሆነ አይገባበትም።
- በንጽሕናና በንስሐ ግቡ፤ ክብሯንም ጠብቁ።

”وَمَنْ يُرِدْ فِيهِ بِإِلْحَادٍ بِظُلْمٍ نُذِقْهُ مِنْ عَذَابٍ أَلِيمٍ“

“በውስጡ በበደል መዘንበልን የሚፈልግ ሰው፣ ከአሳማሚ ቅጣት እናቀምሰዋለን።”

አልሐጅ 22:25፤

- ኢሕራም ያደረገም ሆነ ያላደረገ፣ የሐረምን አደን ማደንና ማባረር፣ በተፈጥሮ የበቀሉ ዕፅዋትን ያለ ሕጋዊ ምክንያት መቁረጥ የለበትም።

- የጠፋ ንብረትን ለራስ መውሰድ አይፈቀድም፤ ለማሳወቅ ወይም ለሚመለከተው አካል ለማስረከብ ቢሆን እንጂ።

አትተውባ 9:28፤ አልቡኻሪ 1834፣ የሐረም ክልከላዎች።

“لَا يُعْضَدُ شَوْكُهُ، وَلَا يُنَفَّرُ صَيْدُهُ، وَلَا يَلْتَقِطُ لُقَطَتَهُ إِلَّا مَنْ عَرَّفَهَا، وَلَا يُخْتَلَى خَلَاهَا”

“የሐረሙ እሾሃማ ዛፎች አይቆረጡ፤ የዱር እንስሳቱም አይበረገጉ። በውስጡ የተገኘን የጠፋ ንብረት፣ ባለቤቱን ለማፈላለግ ከሚያስተዋውቅ ሰው በስተቀር ማንም አያንሳው፤ እርጥብ ሣሩም አይታጨድ።”

አልቡኻሪ 1834

13 / ጠዋፍ

# ወደ መስጂደል ሐረም መግባት




## ቀኝ እግርን አስቀድሙ የመግቢያ ዱዓን ይበሉ

- ቀኝ እግራችሁን አስቀድማችሁ ግቡ፤ በነብዩ ﷺ ላይ ሰላምና በረከት አውርዱ።
- የመግቢያ ዱዓውንም በሉ፦

"اللَّهُمَّ افْتَحْ لِي أَبْوَابَ رَحْمَتِكَ"

"አላሁመ ኢፍተሕ ሊ አብዋበ ረሕመቲክ።"

"ጌታዬ ሆይ፤ የምሕረትህን በሮች ክፈትልኝ።"

ሰሒሕ ሙስሊም 713



- በመስጂደል ሐረም ሶላት የመስገድ ታላቅ ትሩፋት አለ፦

“وَصَلَاةٌ فِي الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ أَفْضَلُ مِنْ مِائَةِ أَلْفِ صَلَاةٍ فِيمَا سِوَاهُ”

“በመስጂደል ሐረም አንድ ሶላት ከእሱ ውጭ ከሚሰገዱ መቶ ሺህ ሶላቶች በላጭ ነው።”

ሱነን ኢብን ማጀህ 1406

- ጊዜያችሁን በሶላት፣ በቁርአን፣ በዚክርና በዱዓ ተጠቀሙበት።

# ጠዋፍን መጀመር



## ሰባት ዙር

- ካዕባን ስታዩ የአላህን ታላቅነት አስታውሱ።
- «የአላህ ቤት» መባሏ ለክብር ነው፤ አላህ ጀልለ ወተዓላ በቤት (ቦታ) የሚወሰን አይደለም።
- ካዕባ የኢብራሂምና የኢስማዒል፣ የሙሐመድ ﷺ እና የተከታዮቻቸውን ታሪክ ታስታውሰናለች።
- ክብሯን በልባችሁ አስቡ፤ አላህንም በትሕትና ለምኑ።
- ጠዋፍን በውዱእ፣ በንጽሕናና ዐውራን በመሸፈን ፈጽሙ።
- ከሐጀረል አስወድ ትይዩ ጀምሩ፤ ካዕባን በግራ ጎናችሁ አድርጋችሁ ሰባት ዙር ዙሩ።
- ሒጅር ኢስማዒልን ከውጭ በኩል አድርጉ።

- ወደ መጀመሪያው ትይዩ ሲመለሱ አንድ ዙር ይሆናል።
- ለወንዶች በዚህ ጠዋፍ ሪዳእን ከቀኝ ብብት ሥር አሳልፎ በግራ ትከሻ ላይ በመደረብ ቀኝ ትከሻን መግለጥ ይወደዳል።
- ይህ በጠዋፍ ጊዜ ብቻ ነው፤ ለሶላት ሁለቱንም ትከሻዎች ይሸፍኑ።

### የጠዋፍ አፈጻጸም:-

“حَتَّى إِذَا أَتَيْنَا الْبَيْتَ مَعَهُ اسْتَلَمَ الرُّكْنَ فَرَمَلَ ثَلَاثًا وَمَشَى أَرْبَعًا”

“ከእርሳቸው ጋር ወደ ካዕባ በደረስን ጊዜ፣ ሐጀረል አስወድን ዳሰሱ። ከዚያም በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዙሮች በአጫጭር እርምጃዎች ፈጠን ብለው ዞሩ፤ በቀሩት አራት ዙሮች ደግሞ በመደበኛ እርምጃ ተራመዱ።”

ሱነን አል ኩብራ 9107

“طَافَ النَّبِيُّ ﷺ مُضْطَبِعًا بِبُرْدٍ أَخْضَرَ”

“ነቢዩ ﷺ አረንጓዴ መጎናጸፊያ ተጎናጽፈው፣ ቀኝ ትከሻቸውን ገልጠው ጠዋፍ አደረጉ።”

አቡ ዳዉድ 1883

15 / ጠዋፍ

# የጠዋፍ ሱናዎች



## ሰባት ዙር

- ሐጀረል አስወድን ሰውን ሳታስቸግሩ መሳም ከቻላችሁ ሳሙት።
- መሳም ካልቻላችሁ በእጅ ንኩት።
- ይህም ካልተቻለ ከሩቅ በቀኝ እጅ አመልክቱና «አላሁ አክበር» በሉ።
- በመጀመሪያው «ቢስሚላህ፣ አላሁ አክበር» ማለትም በፋቀሃዎች ዘንድ ተጠቅሷል።
- ወንዶች ከቻሉ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዙሮች በአጫጭር እርምጃ ፈጠን ብለው ይጓዛሉ፤ በቀሩት አራት ዙሮች መደበኛ እርምጃ ይጠቀማሉ።
- ይህ ረመል (ማረትረት) ይባላል፤ ለሴቶች ሱና አይደለም።

- በመጨናነቅ ጊዜ ሌሎችን አትግፉ ቀስ ብላችሁ ተራመዱ።
- ሩክነል የማኒን መንካት ከቻላችሁ ንኩት፤ ካልቻላችሁ አታመልክቱ። ጠዋፍ በሐጀረል አሰወድ ትይዩ ተጀምሮ በዚያው ትይዩ ይጠናቀቃል።

ሙስሊም 1218፤ አልቡኻሪ 1613፤ ዳር አልኢፍታእ፣ ፈትዋ 7712

“كُلَّمَا أَتَى الرُّكْنَ أَشَارَ إِلَيْهِ بِشَيْءٍ كَانَ عِنْدَهُ وَكَبَّرَ”

“ሐጀረል አሰወድ ወዳለበት ማዕዘን በደረሱ ቁጥር፣ በያዙት ነገር ወደ እርሱ እየጠቆሙ፣ “አላሁ አክበር” ይሉ ነበር።”

አልቡኻሪ 1613

“فَرَمَلَ ثَلَاثًا وَمَشَى أَرْبَعًا”

“ከዚያም በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዙሮች በአጫጭር እርምጃዎች ፈጠን ብለው ዞሩ፤ በቀሩት አራት ዙሮች ደግሞ በመደበኛ እርምጃ ተራመዱ።”

ሱነን አል ኩብራ 9107

# በጠዋፍ ጊዜ የሚባል ዱዓ



### ሩክነል የማኒ ↓ ሐጀረል አሰወድ

- በሩክነል የማኒና በሐጀረል አሰወድ መካከል ይህን ዱዓ በሉ፡-

“رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِي الْآخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ النَّارِ”

“ረበና አቲና ፊድዱንያ ሐሰነተን፣ ወፊል አኺረቲ ሐሰነተን፣ ወቂና ዐዛበንናር።”

“ጌታችን ሆይ፤ በዚህ ዓለም መልካምን ስጠን፣ በመጨረሻውም ዓለም መልካምን ስጠን፣ ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን።”

አልበቀራ 2፡201፤ አቡ ዳዉድ 1892

- በቀሩት የጠዋፍ ሰፍራዎች ቁርአን አንብቡ፣ አላህን አውሱ፣ ለራሳችሁ፣ ለቤተሰቦቻችሁና ለሙስሊሞች ዱዓ አድርጉ።
- በምታውቁት ቋንቋ መለመን ትችላላችሁ።

# በጠዋፍ ጊዜ ማስተንተን



- ካዕባን መዞር ታላቅ ኢባዳ ነው።
- ይህን ጊዜ ለዚክር፣ ለዱዓና ለልብ ንቃት ተጠቀሙበት።
- ከቀድሞ ጥፋታችሁ ለመመለስና ወደ መልካም ለመቅረብ አስቡ።
- በፈጠነ እርምጃ ስትጓዙ ከወንጀል መራቅን፣ ካዕባን በግራ አድርጋችሁ ስትዞሩም ያለፈውን ሕይወታችሁን በመመርመር እውነተኛ ንስሐ መግባትን ልታስቡ ትችላላችሁ።
- ሌሎች ፍጥረታት አላህን እንደሚታዘዙ ሁሉ እናንተም የእሱ ባሪያዎች መሆናችሁን አስታውሱ።
- ለምሳሌ ጊዜያችሁን በኢስቲግፋር፣ በተህሊል፣ ለራስ፣ ለቤተሰብና ለሕዝብ፣ ለዱንያና ለአኺራ ዱዓ በማድረግ ልታቀናጁ ትችላላችሁ።
- ዓላማው ልብን ማንቃትና ጊዜን በመልካም መጠቀም ነው።

ዚክር • ዱዓ • ማስተንተን

# የሐጀረል አሰወድ ትሩፋት



## ሐጀረል አሰወድ ሰውን ሳያስቸግሩ

“نَزَلَ الْحَجَرُ الْأَسْوَدُ مِنَ الْجَنَّةِ وَهُوَ أَشَدُّ بَيَاضًا مِنَ اللَّبَنِ فَسَوَّدَتْهُ خَطَايَا بَنِي آدَمَ”

“ሐጀረል አሰወድ ከወተት ይበልጥ ነጭ ሆኖ ከጀነት ወረደ፤ የአደም ልጆች ኃጢአቶችም አጠቆሩት።”

አትቲርሚዚ 877፤ አትቲርሚዚ ሐሰን ሰሒሕ ብለውታል።

“وَاللَّهِ لَيَبْعَثَنَّهُ اللَّهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ لَهُ عَيْنَانِ يُبْصِرُ بِهِمَا وَلِسَانٌ يَنْطِقُ بِهِ يَشْهَدُ عَلَى مَنِ اسْتَلَمَهُ بِحَقٍّ”

“አላህ በትንሣኤ ቀን በሚያዩ ዐይኖችና በሚናገር ምላስ ያስነሣዋል፤ በእውነት ለነካውም ይመሰክራል።”

አትቲርሚዚ 961

“إِنَّ مَسْحَهُمَا كَفَّارَةٌ لِلْخَطَايَا”

“(ሁለቱን ማዕዘኖች) መንካት የኃጢአት ማበሻ ነው።”

አትቲርሚዚ 959

“إِنِّي أَعْلَمُ أَنَّكَ حَجَرٌ لَا تَضُرُّ وَلَا تَنْفَعُ، وَلَوْلَا أَنِّي رَأَيْتُ النَّبِيَّ ﷺ يُقَبِّلُكَ مَا قَبَّلْتُكَ”

“አንተ የማትጎዳና የማትጠቅም ድንጋይ መሆንህን በእርግጥ አውቃለሁ። ነቢዩ ﷺ ሲስሙህ ባላየሁ ኖሮ፣ እኔም አልሳምህም ነበር።” የሰይዱና ዑመር ንግግር

አልቡኻሪ 1597

- ድንጋዩን የምንስመው የነብዩን ፈለግ በመከተል ነው፤ በራሱ ይጠቅማል ወይም ይጎዳል ብለን አይደለም።

# መቃመ ኢብራሂም እና ሶላት



- ጠዋፍን ስትጨርሱ ወንዶች ቀኝ ትከሻችሁን ሸፍኑ።
- ከተቻለ ከመቃመ ኢብራሂም በስተጀርባ፣ ካልተቻለ በሌላ ተስማሚ ቦታ ሁለት ረከዓ ስገዱ።
- የጠዋፍ መንገድን አትዝጉ።

“وَاتَّخِذُوا مِنْ مَقَامِ إِبْرَاهِيمَ مُصَلًّى”

“ከኢብራሂም መቆሚያ የሶላት ስፍራ አድርጉ።”

አልበቀራ 2:125

- ኢብራሂምና ኢስማዒል ካዕባን ሲገነቡ፣ ግንባታው ከፍ ሲል ኢብራሂም በድንጋይ ላይ ቆመው ይገነቡ ነበር።

- ይህን ታሪክ ማስታወስ የነብያትን ታዛዥነትና ትጋት ያስታውሰናል።
- በመጀመሪያው ረከዓ ከፋቲሐ በኋላ አልካፊሩንን፣ በሁለተኛው አልኢኽላስን ማንበብ ይወደዳል።

የግንባታው ታሪክ፦ አልቡኻሪ 3364፤ የሶላቱ አፈጻጸም፦ ሙስሊም 1218

“فَجَعَلَ إِسْمَاعِيلُ يَأْتِي بِالْحِجَارَةِ وَإِبْرَاهِيمُ يَبْنِي”

“ኢስማዒል ድንጋዮችን ያመጣ ነበር፤ ኢብራሂም ደግሞ ይገነባ ነበር።”

አልቡኻሪ 3364

“فَجَعَلَ الْمَقَامَ بَيْنَهُ وَبَيْنَ الْبَيْتِ”

“መቃመ ኢብራሂምን በእርሳቸውና በካዕባ መካከል እንዲሆን አድርገው ቆሙ።”

ሙስሊም 1218

“كَانَ يَقْرَأُ فِي الرَّكْعَتَيْنِ قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ وَقُلْ يَا أَيُّهَا الْكَافِرُونَ”

“በሁለቱ ረከዓዎች ውስጥ “ቁል ሁወላሁ አሐድ” (ሱረቱል ኢኽላስ) እና “ቁል ያ አዩሃል ካፊሩን” (ሱረቱል ካፊሩን) ያነቡ ነበር።”

ሙስሊም 1218

20 / ጠዋፍ

# ዘምዘም መጠጣት



## ዘምዘም

- ከጠዋፍ ረከዓዎች በኋላ ዘምዘም ጠጡ።
- የአላህን ጸጋ አስታውሱ፤ ለምትፈልጉትም መልካም ነገር ዱዓ አድርጉ።

### ከጠዋፍ በኋላ

ሁለት ረከዓ → ዘምዘም → ሰዕይ

ሙስሊም 1218፤ ፈትዋ 7712 ↗

”مَاءُ زَمْزَمَ لِمَا شُرِبَ لَهُ“

“የዘምዘም ውሃ ለተጠጣለት ዓላማ ይውላል።”

ሱነን ኢብን ማጀህ 3062

- ለጤና፣ ለጠቃሚ ዕውቀት፣ ለጥሩ አምልኮ፣ ለሐላል ሲሳይና ለሌላ መልካም ጉዳይ አላህን ለምኑ።
- ይህ የዱዓና የተወኩል ሰፍራ ነው።
- የዘምዘም ታሪክ ከሃጀር፣ ከኢስማዒልና ከአላህ እርዳታ ጋር ይያያዛል።
- ታሪኩ አላህ በባሪያዎቹ ላይ ያለውን እንክብካቤ እንድናስታውስ ይረዳናል።

የሃጀርና የዘምዘም ታሪክ፦ ሰሒሕ አልቡኻሪ 3364

- ከዚያ ወደ ሶፋ ተጓዙ፤ ሰዕይን ለመጀመር ተዘጋጁ።

”فَبَحَثَ بِعَقِبِهِ - أَوْ قَالَ بِجَنَاحِهِ - حَتَّى ظَهَرَ الْمَاءُ“

“መልአኩ ውኃው እስኪወጣ ድረስ መሬቱን በተረከዙ ቆፈረ፤ ወይም ዘጋቢው “በክንፉ” አለ።”

አልቡኻሪ 3364

21 / ሰዕይ

# በሶፋ እና በመርዋ መካከል ሰዕይ



"إِنَّ الصَّفَا وَالْمَرْوَةَ مِنْ شَعَائِرِ اللَّهِ"

“ሶፋና መርዋ ከአላህ የአምልኮ ምልክቶች ናቸው።”

አልበቀራ 2:158

- ሰዕይን ከጠዋፍ በኋላ በሶፋ ጀምሩ።
- ከሶፋ ወደ መርዋ አንድ ጉዞ ነው፤ ከመርዋ ወደ ሶፋ መመለስ ሁለተኛው ነው።
- በዚህ መልኩ ሰባት ጉዞዎችን በመርዋ ጨርሱ።
- ወንዶች ከቻሉ በሁለቱ አረንጓዴ ምልክቶች መካከል በሶምሶማ ይሂዱ።
- ከምልክቶቹ ውጭ በመደበኛ እርምጃ ይጓዛሉ።
- ሴቶች በመንገዱ ሁሉ በመደበኛ እርምጃ ይጓዛሉ።

- በሰዕይ መንገድ ሁሉ መሮጥ አያስፈልግም።
- በእርጋታ ቁጠሩ።
- አንድ መሄድና መመለስን አንድ ብላችሁ አትቁጠሩ።

“حَتَّى إِذَا انْصَبَّتْ قَدَمَاهُ فِي بَطْنِ الْوَادِي سَعَى حَتَّى إِذَا صَعِدَتَا مَشَى حَتَّى أَتَى الْمَرْوَةَ”

“ወደ ሸለቆው ግርጌ በወረዱ ጊዜ ሮጡ፤ ከሸለቆው ወደ ላይ ሲወጡ ደግሞ፣ መርዋ እስኪደርሱ ድረስ ተራመዱ።”

ሙስሊም 1218

## የሰዕይ ሰባቱ ጉዞዎች




መነሻ፦ ሶፋ | መጨረሻ፦ መርዋ

እያንዳንዱ የአንድ አቅጣጫ ጉዞ አንድ ነው።

ሙስሊም 1218 ↗

22 / ሰዕይ

# የሶፋ እና የመርዋ ዚክር



- ወደ ሶፋ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀርቡ ያለፈውን አንቀጽ አንብቡ።
- «አብደኡ ቢማ በደአላሁ ቢህ»፣ ማለትም «አላህ በጀመረበት እጀምራለሁ» በሉ።
- ቂብላን ተመልክታችሁ፣ እጆቻችሁን ለዱዓ አንሥታችሁ አላህን አወድሱ፣ ተክቢርም በሉ።

“لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللَّهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللَّهُ وَحْدَهُ أَنْجَزَ وَعْدَهُ وَنَصَرَ عَبْدَهُ وَهَزَمَ الْأَحْزَابَ وَحْدَهُ”

“ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም። ብቻውን ነው፤ አጋር የለውም። ንግሥናና ምስጋና የእሱ ናቸው፤ በሁሉ ቻይ ነው። ቃሉን ፈጸመ፣ ባሪያውን ረዳ፣ ተባባሪ ጠላቶችንም ብቻውን አሸነፈ።”

ሰሒሕ ሙስሊም 1218

- ዚክሩን ሦስት ጊዜ በሉ፣ በመካከሉም ዱዓ አድርጉ።
- በመርዋም እንዲሁ አድርጉ፤ አንቀጹን መድገም ግን አያስፈልግም።

ዚክር በሶፋና በመርዋ

# የሰዕይ ዚክር የንባብ እገዛ



- የሶፋና የመርዋ ዚክርን በአማርኛ ፊደል ለማንበብ የሚከተለውን ይጠቀሙ።
- ዐረብኛውን ከመሪው ጋር ተለማመዱ።

“ላ ኢላሀ ኢለላሁ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለህ።”

“ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ፣ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር።”

“ላ ኢላሀ ኢለላሁ ወሕደህ።”

“እንጀዘ ወዕደሁ፣ ወነሶረ ዐብደሁ፣ ወሀዘመል አሕዛበ ወሕደህ።”

- ለራሳችሁ፣ ለቤተሰቦቻችሁና ለሙስሊሞች መልካምን ለምኑ።
- የዚክርና የዱዓ ጊዜውን በእርጋታና በልብ ተሳትፎ ተጠቀሙበት።

# ሰዕይ እና የተሰፋ ትምህርት



- ሃጀር ለልጃቸው ውሃ ፍለጋ በሶፋና በመርዋ መካከል መጓዛቸው፣ አላህም ዘምዘምን ማፍለቁ፣ የጥረትና የተወኩል ታላቅ ትምህርት ነው።

ሰሒሕ አልቡኻሪ 3364።

- በሰዕይ ጊዜ ከተሰፋ መቁረጥ መራቅን፣ የጠፋውን መልካም ለመመለስ መጣርን፣ ወንጀልን ወደ ኋላ ትቶ ወደ አላህ ውዴታ መሄድን አስቡ።
- አላህን ተማመኑ፣ በርሱም ተወከሉ።

## ለሴቶች ማስታወሻ

- የወር አበባ ያለባት ሴት ከዚያ በፊት ትክክለኛ ጠዋፍ ከፈጸመች ሰዕይ ማድረግ ትችላለች።
- ጠዋፍን ሳትፈጽም ግን ሰዕይን አታስቀድም።
- ዝርዝሩን ከሃይማኖት መሪው ጋር አረጋግጡ።

“فَلَا يَصِحُّ السَّعْيُ إِلَّا بَعْدَ طَوَافٍ”

“ሰዕይ ከጠዋፍ በኋላ ካልተደረገ ትክክል አይሆንም።”

አሸሺራዚ፣ አልሙሀዝዘብ፤ አንነወዊ፣ አልመጅሙዕ፣ የሰዕይ ምዕራፍ።

“فَفَعَلْتُ ذَلِكَ سَبْعَ مَرَّاتٍ. قَالَ ابْنُ عَبَّاسٍ قَالَ النَّبِيُّ ﷺ فَذَلِكَ سَعْيُ النَّاسِ بَيْنَهُمَا”

“እርሷም ይህንን ሰባት ጊዜ አደረገች። ኢብን ዐባስ እንዳሉት፣ ነቢዩ ﷺ፦ “ሰዎች በሁለቱ መካከል የሚያደርጉት ሰዕይ መነሻ ይህ ነው” ብለዋል።”

አልቡኻሪ 3364

# ፀጉር መቁረጥ እና መፈታት



## ከሰዕይ በኋላ

- የመጨረሻው የዑምራ ተግባር ሰዕይን ካጠናቀቁ በኋላ ፀጉር መላጨት ወይም ማሳጠር ነው።

## ለወንዶች

- ወንዶች ራሳቸውን ይላጫሉ ወይም ፀጉራቸውን ያሳጥራሉ።
- ማሳጠርን ከመረጡ ከመላው ራስ ማሳጠር ከመዝሀብ ልዩነት ለመውጣት ይረዳል።

## ለሴቶች

- ሴቶች አይላጩም፤ ከፀጉራቸው ጫፍ ትንሽ ይቆርጣሉ።

- የጣት አንጓ ያህል መቁረጥ ይመከራል።
- ይህን በተሸፈነ ቦታ ያድርጉ።
- ይህን ካደረጋችሁ ዑምራችሁ ይጠናቀቃል።
- ከኢሕራም ትፈታላችሁ፤ በኢሕራም ምክንያት የተከለከሉ ነገሮችም ይፈቀዳሉ።
- የሐረም ክብርና የቦታው ክልከላዎች ግን ይቀጥላሉ።

“اللَّهُمَّ ارْحَمِ الْمُحَلِّقِينَ ... وَالْمُقَصِّرِينَ”

“አላህ ሆይ! የራስ ፀጉራቸውን ለተላጩት እዝነት አድርግላቸው፤ ... ፀጉራቸውን ላሳጠሩትም እንዲሁ።”

አልቡኻሪ 1727

“لَيْسَ عَلَى النِّسَاءِ حَلْقٌ إِنَّمَا عَلَى النِّسَاءِ التَّقْصِيرُ”

“ሴቶች የራስ ፀጉራቸውን አይላጩም፤ ለእነርሱ የተደነገገው ፀጉራቸውን ማሳጠር ብቻ ነው።”

አቡ ዳዉድ 1984

# ለሴቶች እና ለቡድን ተጓዦች



## የወር አበባ እና የወሊድ ደም

- በእነዚህ ሁኔታዎች ኢሕራም ማድረግ፣ ተልቢያ ማለትና ዱዓ ማድረግ ይቻላል።
- ጠዋፍ ግን ንጹሕ እስኪሆኑና ገላን እስኪታጠቡ አያደርጉም።
- የመመለሻ ቀን ከቀረበ አስቀድማችሁ መሪውን አማክሩ።

“افْعَلِي كَمَا يَفْعَلُ الْحَاجُّ غَيْرَ أَنْ لَا تَطُوفِي بِالْبَيْتِ حَتَّى تَطْهُرِي”

“ሐጅ አድራጊው የሚያደርገውን ሁሉ አድርጊ፤ ነገር ግን ከወር አበባሽ እስክትጠሪ ድረስ በካዕባ ጠዋፍ አታድርጊ።”

አልቡኻሪ 1650

# ከቡድኑ ጋር መቆየት

- የሆቴል ካርድ፣ የመሪው ስልክና የመገናኛ ቦታ መረጃ ይያዙ።
- የመስጂዱን መግቢያ በር ቁጥር ያስታውሱ።
- ከተለያያችሁ ለመሪው ይደውሉ ወይም ወደ ተስማማችሁበት ቦታ ሂዱ።
- አረጋውያንንና የእርዳታ ፈላጊዎችን እርዱ።
- ከክርክር ራቁ፤ ንጽሕናንና የሌሎችን መብት ጠብቁ።
- ስለ ኢባዳችሁ እርግጠኛ ካልሆናችሁ ከመገመት ይልቅ ዐሊምን ጠይቁ።

# የዑምራ አጭር ማጠቃለያ



| 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|
| ኢሕራም | ጠዋፍ | ሰዕይ | ፀጉር |

## 1 ኢሕራም

- ሚቃትን ከማለፍ በፊት ኒያ አድርጉ።
- ተልቢያን ቀጥሉ፣ የኢሕራምንም ክልከላዎች ጠብቁ።

## 2 ጠዋፍ

- በውዱእና በንጽሕና ካዕባን በግራ አድርጋችሁ ሰባት ዙር ዙሩ።
- ከዚያ ሁለት ረከዓ ሰገዱ፣ ዘምዘምም ውሃ ጠጡ።



## 3 ሰዕይ

- በሶፋ ጀምሩ፤ በመርዋ ጨርሱ።
- መሄድ አንድ፣ መመለስ ሁለት ነው።
- በድምሩ ሰባት ጉዞዎችን አጠናቅቁ።

## 4 ፀጉር መቁረጥ

- ወንዶች ይላጩ ወይም ያሳጥሩ።
- ሴቶች ከፀጉራቸው ጫፍ ይቁረጡ።
- ከዚያ ከኢሕራም ትፈታላችሁ።
- አላህ ዑምራችሁን ይቀበላችሁ።

# የጉዞ ማረጋገጫ እና ማስታወሻ



## የጉዞ ዝግጅት

### ከመነሳታችሁ በፊት

- የጉዞ ሰነዶችንና ቅጂዎቻቸውን፣ የመሪውን ስልክ፣ የኢሕራም ልብስ፣ የግል ዕቃዎችንና በመደበኛነት የምትጠቀሙባቸውን መድኃኒቶች አረጋግጡ።
- የጉዞ ቀንና ሰዓትን ከቃፊላ የጉዞ ወኪል ጋር አረጋግጡ።

# የተመረጡ ዱዓዎች

29 / ዱዓ

## 1. የደከመ ልብ ጥሪ



“اللَّهُمَّ، جِئْتُ إِلَى بَيْتِكَ بِقَلْبٍ أَتْعَبَتْهُ الْحَيَاةُ، فَأَرِحْهُ بِقُرْبِكَ، وَبِذُنُوبٍ أَثْقَلَتْنِي، فَخَفِّفْ عَنِّي بِعَفْوِكَ، وَبِرَجَاءٍ فِي رَحْمَتِكَ، فَلَا تَحْرِمْنِي فَضْلَكَ.”

“አላህ ሆይ! ሕይወት ያደከመውን ልብ ይዤ ወደ ቤትህ መጥቻለሁ፤ ወደ አንተ በመቅረብ አሳርፈው። ያከበዱኝን ኃጢአቶች ይዤ መጥቻለሁ፤ በይቅርታህ ሸክሜን አቅልልልኝ። እዝነትህን ተስፋ አድርጌ መጥቻለሁ፤ ችሮታህን አትከልክለኝ።”

# 2. በቃላት ያልተገለጡ ሐጃዎች



“يَا رَبِّ، فِي قَلْبِي حَاجَاتٌ لَمْ أُحْسِنِ التَّعْبِيرَ عَنْهَا، وَأَنْتَ تَعْلَمُهَا، فَاقْضِ لِي مِنْهَا مَا فِيهِ خَيْرِي، وَاصْرِفْ عَنِّي مَا يَضُرُّنِي، وَارْزُقْنِي الرِّضَا بِمَا تَخْتَارُهُ لِي.”

“ጌታዬ ሆይ! በልቤ ውስጥ በቃላት በሚገባ ልገልጻቸው ያልቻልኩ ሐጃዎች አሉ፤ አንተ ግን ታውቃቸዋለህ። መልካም የሆኑልኝን ፈጽምልኝ፤ የሚጎዳኝንም ከእኔ አርቅ። በምትመርጥልኝም እንድረካ አድርገኝ።”

# 3. ለአዲስ ጅማሮ



“اللَّهُمَّ، اجْعَلْ هَذِهِ الرِّحْلَةَ بِدَايَةَ صِدْقٍ مَعَكَ،
وَاغْفِرْ لِي مَا مَضَى، وَأَصْلِحْ لِي مَا بَقِيَ، وَأَعِنِّي إِذَا
ضَعُفْتُ، وَرُدَّنِي إِلَى طَاعَتِكَ إِذَا زَلَلْتُ.”

“አላህ ሆይ! ይህን ጉዞ ከአንተ ጋር በእውነት የመኖር ጅማሮ አድርግልኝ። ያለፈውን ማረኝ፤ የቀረውን ሕይወቴንም አስተካክልልኝ። ስደክም እርዳኝ፤ ስሳሳትም ወደ መታዘዝህ መልሰኝ።”

# 4. የሕይወት ጥረት ፍሬ እንዲያፈራ



“اللَّهُمَّ، كَمَا أَعَنْتَنِي عَلَى السَّعْيِ بَيْنَ الصَّفَا وَالْمَرْوَةِ، فَأَعِنِّي عَلَى السَّعْيِ فِي رِضَاكَ، وَبَارِكْ لِي فِي جُهْدِي، وَاجْعَلْ تَعَبِي فِي الْخَيْرِ سَبَبًا لِفَرَجٍ تَقَرُّ بِهِ عَيْنِي.”

“አላህ ሆይ! በሰፋና በመርዋ መካከል ሰዕይ እንዳደርግ እንደረዳኸኝ፣ ውዴታህን ፍለጋ እንድተጋም እርዳኝ። ጥረቴን ባርክልኝ፤ ለበጎ ነገር የደከምኩትንም ዐይኔ የሚቀዘቅዝበት ደስታ ምክንያት አድርግልኝ።”

# 5. የወላጆችን ውለታ በዱዓ ማስታወስ



“اللَّهُمَّ، اجْزِ وَالِدَيَّ عَنِّي خَيْرَ الْجَزَاءِ، وَاغْفِرْ لَهُمَا، وَارْحَمْ ضَعْفَهُمَا، وَبَارِكْ لِلْحَيِّ مِنْهُمَا فِي عُمُرِهِ وَعَمَلِهِ، وَآنِسْ وَحْشَةَ مَنْ مَاتَ مِنْهُمَا، وَاجْمَعْنَا فِي جَنَّتِكَ.”

“አላህ ሆይ! ወላጆቼን በእኔ ምክንያት ከሁሉ የተሻለ ምንዳ ስጣቸው። ማራቸው፤ ድካማቸውንም እዘንላቸው። በሕይወት ላለው ዕድሜውንና ሥራውን ባርክ፤ ለሞተውም ብቸኝነቱን አስወግድለት። በጀነትህም አንድ ላይ ሰብስበን።”

# 6. ለቤተሰብ ሰላምና ለልጆች መልካምነት



“اللَّهُمَّ، أَصْلِحْ أَهْلِي وَذُرِّيَّتِي، وَاجْعَلْ بُيُوتَنَا عَامِرَةً بِالْمَوَدَّةِ وَالرَّحْمَةِ، وَعَلِّمْنَا حُسْنَ الْإِنْصَاتِ وَالْعَفْوِ وَالرِّفْقِ، وَاجْعَلْ لِأَوْلَادِنَا مِنْ دُعَائِنَا نَصِيبًا، وَمِنْ هِدَايَتِكَ نُورًا.”

“አላህ ሆይ! ቤተሰቤንና ዘሮቼን መልካም አድርግልኝ። ቤቶቻችንን በፍቅርና በእዝነት ሙላቸው። እርስ በርስ በጥሞና ማዳመጥን፣ ይቅር መባባልንና መለሳለስን አስተምረን። ለልጆቻችን ከዱዓችን ድርሻ፣ ከምሪትህም ብርሃን አድርግላቸው።”

# 7. ለዕዳ፣ ለኑሮ ጭንቀትና ለሐላል ሲሳይ



“اللَّهُمَّ، أَنْتَ تَعْلَمُ مَا أَثْقَلَنِي مِنْ دَيْنٍ، وَمَا أَقْلَقَنِي مِنْ هَمِّ الرِّزْقِ؛ فَاقْضِ دَيْنِي، وَافْتَحْ لِي رِزْقًا حَلَالًا مُبَارَكًا، وَارْزُقْنِي قَلْبًا قَانِعًا، وَيَدًا كَرِيمَةً تُعْطِي.”

“አላህ ሆይ! ያከበደኝን ዕዳና ያስጨነቀኝን የኑሮ ሐሳብ ታውቃለህ። ዕዳዬን ክፈልልኝ፣ ሐላልና የተባረከ ሲሳይ ክፈትልኝ። የሚረካ ልብና ለሌሎች የሚሰጥ ለጋስ እጅ ስጠኝ።”

# 8. ለታመሙ ሰዎችና ለአስታማሚዎቻቸው



“اللَّهُمَّ، اشْفِ أَجْسَادًا أَتْعَبَهَا الْمَرَضُ، وَقُلُوبًا أَرْهَقَهَا الْخَوْفُ، وَارْزُقِ الْمَرْضَى أَمَلًا وَسَكِينَةً، وَأَعِنْ مَنْ يَسْهَرُونَ عَلَى رَاحَتِهِمْ، وَاجْعَلْ لَهُمْ جَمِيعًا مِنْ لُطْفِكَ نَصِيبًا.”

“አላህ ሆይ! በሽታ ያደከማቸውን አካላትና ፍርሃት ያስቃያቸውን ልቦች ፈውስ። ለታማሚዎች ተስፋና እርጋታ ስጥ። ለእረፍታቸው ሲሉ የሚያድሩትንም እርዳቸው፤ ሁሉንም በርኅራኄህ አካብባቸው።”

# 9. ዱዓ እንድናደርግላቸው ለጠየቁን



“اللَّهُمَّ، كُلُّ مَنْ سَأَلَنِي الدُّعَاءَ، وَكُلُّ مَنْ أَحْسَنَ إِلَيَّ، وَكُلُّ مَنْ أَحَبَّ لِيَ الْخَيْرَ، فَاذْكُرْهُ بِرَحْمَتِكَ، وَاقْضِ حَاجَتَهُ، وَإِنْ نَسِيتُ اسْمَهُ فَأَنْتَ تَعْلَمُهُ وَلَا تَنْسَاهُ.”

“አላህ ሆይ! ዱዓ እንዳደርግለት የጠየቀኝን ሁሉ፣ በጎ ያደረገልኝን ሁሉ፣ መልካም ነገር የተመኘልኝን ሁሉ በእዝነትህ አስታውሰው፤ ሐጃውንም ፈጽምለት። እኔ ስሙን ብረሳም፣ አንተ ታውቀዋለህ፤ አትረሳውም።”

# 10. ለተበደሉ፣ ለተፈናቀሉና ለተራቡ



“اللَّهُمَّ، لِي إِخْوَةٌ لَا أَعْرِفُ أَسْمَاءَهُمْ، وَأَنْتَ تَعْلَمُ آلَامَهُمْ؛ فَأَطْعِمْ جَائِعَهُمْ، وَآمِنْ خَائِفَهُمْ، وَآوِ مُشَرَّدَهُمْ، وَانْصُرْ مَظْلُومَهُمْ، وَرُدَّ إِلَى قُلُوبِهِمُ الطُّمَأْنِينَةَ.”

“አላህ ሆይ! ስማቸውን የማላውቃቸው ወንድሞችና እህቶች አሉኝ፤ አንተ ግን ሕመማቸውን ታውቃለህ። የተራበውን አብላ፣ የፈራውን አረጋጋ፣ ለተፈናቀለው መጠለያ ስጥ፣ የተበደለውን እርዳ፤ እርጋታንም ወደ ልባቸው መልስ።”

# 11. ለማይታወቀው ነገ አላህን መታመን



“يَا رَبِّ، لَا أَعْلَمُ مَا يَنْتَظِرُنِي، وَلَكِنِّي أَعْلَمُ أَنَّ رَحْمَتَكَ وَاسِعَةٌ، فَاخْتَرْ لِي مَا يُصْلِحُنِي، وَعَلِّمْنِي أَنْ أَسْعَى بِاجْتِهَادٍ، وَأَنْتَظِرَ بِصَبْرٍ، وَأَتَلَقَّى عَطَاءَكَ بِشُكْرٍ.”

“ጌታዬ ሆይ! ወደፊት ምን እንደሚጠብቀኝ አላውቅም፤ እዝነትህ ሰፊ መሆኑን ግን አውቃለሁ። የሚያስተካክለኝን ምረጥልኝ። በትጋት መሥራትን፣ በትዕግሥት መጠበቅንና ስጦታህን በምስጋና መቀበልን አስተምረኝ።”

# 12. ከዑምራ በኋላ የሚቀጥል ለውጥ



“اللَّهُمَّ، تَقَبَّلْ عُمْرَتِي، وَرُدَّنِي إِلَى أَهْلِي سَالِمًا، وَاجْعَلْ أَثَرَ هَذِهِ الرِّحْلَةِ بَاقِيًا فِي صَلَاتِي وَأَخْلَاقِي وَمُعَامَلَتِي، وَإِذَا ابْتَعَدْتُ عَنْ بَيْتِكَ فَلَا يَبْتَعِدْ قَلْبِي عَنْ ذِكْرِكَ.”

“አላህ ሆይ! ዑምራዬን ተቀበለኝ፤ ወደ ቤተሰቤም በሰላም መልሰኝ። የዚህ ጉዞ አሻራ በሶላቴ፣ በሥነ ምግባሬና ከሰዎች ጋር ባለኝ ግንኙነት ውስጥ እንዲቀጥል አድርግ። ከቤትህ ብርቅም፣ ልቤ አንተን ከማስታወስ አይራቅ።”

አሚን አሚን አሚን!

ማጣቀሻዎች

# ቁርአንና የምንጭ አጠቃቀም

በመመሪያው ውስጥ ያሉ የአረብኛ ጥቅሶችንና ሪፈረንሶቻቸውን በመንካት ምንጮቹን መክፈት ይችላሉ። ማስፈንጠሪያዎቹን ለመክፈት የኢንተርኔት ግንኙነት ያስፈልጋል።

**ቁርአን**

القرآن الكريم

በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ አንቀጾች፦

2:125 2:158 2:201 9:28 22:25

የኒያ መግለጫ ሐረጎች የአጠቃቀም ምሳሌዎች ናቸው። በመጨረሻ የቀረቡት 12 ዱዓዎች የግል ልመናዎች ናቸው፤ እንደ ቁርአን ወይም እንደ ሐዲስ ጥቅስ አልተቀረቡም።

የፊቅህ ጥቅሱ ከአሽሺራዚ አልሙህዝዘብ የተወሰደ፣ በአንነወዊ አልመጅሙዕ ውስጥ የተብራራ ነው።

ማጣቀሻዎች

# ሰሒሕ የሐዲስ ስብስቦች

## ሰሒሕ አልቡኻሪ

صحيح البخاري

ኢማም ሙሐመድ ኢብን ኢስማዒል አልቡኻሪ። የተጠቀሱ የሐዲስ ቁጥሮች፦

1524 · 1531 · 1539 · 1549 · 1597 · 1613 · 1650 · 1727 · 1785 · 1834 · 1838 · 3364 · 5889

## ሰሒሕ ሙስሊም

صحيح مسلم

ኢማም ሙስሊም ኢብን አልሐጃጅ። ሐዲስ 1218 የጃቢርን ዝርዝር የሐጅ ዘገባ ይዟል።

443 · 713 · 1218 · 1297 · 1409

ማጣቀሻዎች

# ሱነንና ጃሚዕ

## ጃሚዕ አትቲርሚዚ

جامع الترمذي

ኢማም ሙሐመድ ኢብን ዒሳ አትቲርሚዚ።

828 877 959 961

## ሱነን አቢ ዳዉድ

سنن أبي داود

ኢማም አቡ ዳዉድ ሱለይማን ኢብን አልአሽዐሥ።

1883 1892 1984

## ሱነን ኢብን ማጀህ

سنن ابن ماجه

ኢማም ሙሐመድ ኢብን የዚድ ኢብን ማጀህ።

1406 3062

ማጣቀሻዎች

# ተጨማሪ የሐዲስ ምንጮች

## አስሱነን አልኩብራ

السنن الكبرى للبيهقي

ኢማም አሕመድ ኢብን አልሑሰይን አልበይሀቂ። ሐዲስ 9107፣ የጠዋፍ ረከዓዎች ምዕራፍ።

ምንጩን ክፈት ↗

## አልሙዕጀም አልአውሰጥ

المعجم الأوسط للطبراني

ኢማም ሱለይማን ኢብን አሕመድ አጥጠበራኒ። ሐዲስ 7779፣ ቅጽ 7፣ ገጽ 379። ማስፈንጠሪያው በአድዱረር አስሰኒያ የቀረበውን ዋና ጽሑፍ ይከፍታል።

ምንጩን ክፈት ↗

## አስሲልሲላ አስሰሒሐ

سلسلة الأحاديث الصحيحة

ሸይኽ ሙሐመድ ናሲሩዲን አልአልባኒ። ሐዲስ 1621። የተልቢያና የተክቢር ትሩፋት ሐዲስ ማጣቀሻ።

ምንጩን ክፈት ↗

ማጣቀሻዎች

# ፊቅህና ፈትዋዎች

### አልመጅሙዕ ሸርሕ አልሙህዝዘብ

المجموع شرح المهذب

ኢማም የሕያ ኢብን ሸረፍ አንነወዊ። የሰዕይ ምዕራፍ፣ በማትኑ ውስጥ ያለው ጥቅስ የኢማም አቡ ኢስሐቅ አሽሺራዚ ነው።

ምንጩን ክፈት ↗

### ዳር አልኢፍታእ አልሚስሪያ

حكم صلاة ركعتين عند الإحرام

ፈትዋ 7516፣ 2 ማርች 2023። የኢሕራም ሁለት ረከዓዎች ሥርዓት።

ምንጩን ክፈት ↗

### ዳር አልኢፍታእ አልሚስሪያ

بيان سنن العمرة وحكم من تركها

ፈትዋ 7712፣ 20 ጁን 2023። የዑምራ ሱናዎችና የተዋቸው ሰው ሁኔታ።

ምንጩን ክፈት ↗

# QAFILA

Qafila Tour & Travel



## ቃፊላ የጉዞ ወኪል

0938383802

0970707011

አድራሻ፡ ጀሞ 1 ከለላ ህንጻ 4ኛ ፎቅ

↩ ማውጫ